# ከኢሚግሬሽን አፈጻጸም ጋር የተያያዙ መብቶችዎን ይወቁ

## ፍተሻ እንዲያካሂዱ ፈቃድ አይስጡ

በዳኛ የተፈረመ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልያዙ በስተቀር የኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖች ወይም ፖሊስ ወደ መኪናዎ ወይም ሰውነትዎ እንዲገቡ ወይም እንዲፈትሹ ፈቃድ የመከልከል መብት አለዎት።

## ዝም ይበሉ እንዲሁም ምንም ነገር አይፈርሙ

ያለመናገር መብት አለዎት። ጠበቃ ሳይኖር ምንም ዓይነት ጥያቄዎች እንደማይመልሱ ወይም ሰነዶች ላይ እንደማይፈርሙ ጮክ ብለው በግልጽ ይናገሩ።

## በሩን አይክፈቱ

በመስኮት ወይም በተዘጋ በር በኩል ያነጋግሩ። ኢሚግሬሽን ወደ ቤትዎ መግባት የሚችለው በዳኛ የተፈረመ የእስር ማዘዣ ካለ ብቻ ነው።

## ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች እና/ወይም ማስታወሻዎች ይያዙ

የመቅረጽ/መቅዳት መብትዎን እንደሚጠቀሙ ለመኮንኑ ያሳውቁ። ፎቶዎችን ያንሱ፣ ግንኙነቱን ይቅረጹ/ይቅዱ እና ዝርዝሮቹን ይፃፉ።

## የICE እንቅስቃሴን ወደ ማህበረሰብ የስልክ መስመር በመደወል ሪፖርት ያድርጉ

PIRC የኢሚግሬሽን እንቅስቃሴን የሚያረጋግጡና የሚመዘግቡ እና ለተጎጂዎች ድጋፍ የሚሰጡ ፈጣን ምላሽ ሰጪ ቡድኖችን ያነጋግራል።

## ዜናዎችን እና ጭምጭምታዎችን ያረጋግጡ

ይህ ፍርሃትን ብቻ ስለሚፈጥር ያልተረጋገጡ መረጃዎችን አያጋሩ። ስለ ICE ዜና የሚያጋሩ ሰዎችን ምንጮቻቸውን እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፤ ምስክሮቹንም ወደ PIRC ደውለው እንዲያረጋግጡ ያሳውቁ።

PIRC
PORTLAND IMMIGRANT RIGHTS COALITION

## የPIRC የስልክ መስመር፦
## 1-888-622-1510